# የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት ስርጭት እና አመላለስ የአፈጻፀም መመሪያ ቁጥር 18/2012

Implementation Guide for the Provision, Distribution, and Transfer of Agricultural Input Loans (Directive No. 18/2012)


ግብርና ሚኒስቴር
Ministry of Agriculture


ሐምሌ 21፥ 2012

## ማውጫ


1. መግቢያ ... 2
2. የመመሪያዉ ዓላማ እና አስፈላጊነት ... 3
   2.1. ዓላማ ... 3
   2.2. አስፈላጊነት ... 3
3. የነባሩ ግብርና ግብዓት ብድር አስተዳደር ስርዓት መሰረታዊ ችግሮች ... 4
4. የአዲሱ የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ሥርጭት እና አመላለስ ስርዓት ... 7
   4.1. አጠቃላይ ... 7
   4.2. የአዲሱ የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ሥርጭት እና አመላለስ ስርዓት መርሆች 7
   4.3. የአዲሱ የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ስርጭትና አመላለስ ስርዓት ማብራሪያ ... 9
   4.4. የአዲሱ የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ስርጭትና አመላለስ የስራ ፍሰት ... 12
   4.5. ከአዲሱ የግብርና ግብዓት ብድር ሥርዓት የሚጠበቁ ውጤቶች ... 14
5. በግብዓት ብድር አስተዳደር ስርዓት የባለድርሻ አካላት ተግባር እና ኃላፊነት ... 15
6. ማጠቃለያ ... 26

1. መግቢያ

የአገራችንን የግብርና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የግብርና ግብዓት አጠቃቀምን ማሳደግ አማራጭ የሌለዉ ተግባር ነዉ። አርሶ አደሩ ምርትና ምርታማነቱን ለማሳደግ የግብርና ግብዓቶችን በሚመከረው መጠን መጠቀም አለበት። በተለያዩ ጥናቶች እና ከባለፉት ዓመታት ተሞክሯችንለማየት እንደተቻለው በበቂ ሁኔታ፣ በተደራጀ እና ግልጽ የስራ ሂደትብድርን ለአርሶ አደሮች ማቅረብ የግብርና ግብዓቶችን በሚመከረው መጠን አርሶ አደሩ እንዲጠቀም ይረዳል። ይህንን ለእድገትና ትራንስፎርሜሽን ወሳኝ ሚና ያለውን ተግባር ከዳር ለማድረስ መንግስት የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ሥርጭትና አመላለስ ሥርዓት ለማሻሻል አዲስ መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል። ይኸውም በዚሁ ረገድ በፌደራል ደረጃ፣ በክልል መንግስታትና በግብርና ሚኒስቴር በኩል በየክልሉ የግብርና ግብዓት አጠቃቀምን ለማሳደግ የሚደረገውን ከፍተኛ ጥረት የሚያግዝ ይሆናል።

የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ከማሳደግና መንግስት ካለው ኃላፊነት አንጻር የየክልሉን በጀት በዋስትናነት በማሲያዝ ከባንክ ብድር እንዲፈቀድ በማድረግ በዩኔዬኖች በኩል የግብርና ግብዓቱ እንዲሰራጭ እያደረገ ይገኛል። ይሁን እንጂ በአገራችን የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ስርጭትና የብድር አመላለስ የአሰራር ስርዓት ዉስጥ በርካታ ችግሮች ሲከሰቱ ይስተዋላል። ይኸውም በዋናነኝነት የማይመለስ የብድር መጠንንበከፍተኛ ሁኔታ እንዲያድግ አስተዋጾ አድርጓል። በመሆኑም የክልሎች ዕቅድ አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡ ለአብነትም አርሶ አደሩ የተበደረውን ብድር በወቅቱ ሳይመልስ ሲቀር፤እንዲሁም በኅብረት ሥራ ማህበራት ከአ/አደሩ የሚሰበሰብ የግብርና ግብዓት የብድር ገንዘብ በአግባቡ እና በወቅቱ ለአበዳሪ ተቋማት ገቢ ባለመደረጉ እናአበዳሪ ተቋማት የተጣለባቸውን የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት ባለመወጣታቸዉ የኢትዮጵያንግድ ባንክ በዋስትናነት የያዘውን የክልሎችን በጀት በመቀነስ ወደ ካዝናው ያስገባል። የየክልሎች በጀት ሲቀነስም በያዙት የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖያሳድራል። ከዚህም ሌላ አርሶ አደሩ መጠቀም የሚገባዉን የግብርና ግብዓት እየተጠቀመ አይደለም።

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሰዉን የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ስርጭትና የብድር አመላለስ የአሰራር ስርዓት አገራዊ ችግር ለመፍታት በግብርና ሚኒስቴር የዓመቱ ቁልፍ ተግባር አድርጎ በመያዝ ይህንን የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ስርጭትና አመላለስ ስርዓት መመሪያ በማዉጣት ተግባራዊ ማድረግ አስፈልጓል፡፡

## 2. የመመሪያዉ ዓላማ እና አስፈላጊነት

### 2.1. ዓላማ

የተስተካከለ፣ቀልጣፋ እና ቀጠይነት ያለዉ የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ስርጭት እና አመላለስ ስርዓት በመገንባት የዘርፉን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የአገሪቱን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ነዉ፡፡

### 2.2. አስፈላጊነት

የተያዘውን የእድገት፣ ትራንስፎርሜሽንና የህዳሴ ጉዞ በዘላቂነትና በውጤታማነት በሚፈለገው ፍጥነት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መገንባት በማስፈለጉ ይህ የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ስርጭት እና አመላለስ ስርዓት መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## 3. የነባሩ ግብርና ግብዓት ብድር አስተዳደር ስርዓት መሰረታዊ ችግሮች

የግብርና ግብዓት ለምርትና ምርታማነት አስፈላጊ በመሆኑ በቂ ትኩረት እንዲሰጠው የሚያስችሉ አደረጃጀቶችና ምቹ ፖሊሲ ያሉ ቢሆንም የግብርና ግብዓት አጠቃቀም ለበርካታ ዓመታት የሚፈለገውን ያህል እየጨመረ ሲሄድ አልተስተዋለም፡፡

ይህም አዝጋሚ የግብርና ግብዓት አጠቃቀም ዕድገት ሊከሰት የቻለው አንድም ለግብዓት መግዣ የሚውል ብድር በበቂ መጠንና በወቅቱ መቅረብ ባለመቻሉ፣ በሌላ በኩል የሚቀርበውም የብድር ገንዘብ በወቅቱ እና በበቂ መጠን ለአበዳሪው አካል ሊመለስ ባለመቻሉ እንደሆነ ይታወቃል፤

ባለፉት በርካታ ዓመታት ሲሰራበት የነበረዉ የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ስርጭት እና አመላለስ ሂደት መሰረታዊ ፍሰት ችግሮች ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል።

3.1. አርሶ አደሩን ለመበደር የሚያበቁ መስፈርቶችን ሊያሟላ በሚችልበት አኳኋን የሚሰሩ የአበዳሪ የፋይናንስ ተቋማት ተደራሽ ተደራሽ አለመሆን፤

3.2. ከዚህ ጋር ተያይዞ መንግስት ልማቱን ለማስቀጠል የሚያስችል የግብዓት አጠቃቀም እንዲኖር ለማድረግ ለግብርና ግብዓት መግዣ የሚሆን ብድር በዩኔኖች በኩል ለአበዳሪ ድርጅቶች የየክልሎችን በጀት ዋስትና በመስጠት ግብዓቱ እንዲገዛ ጥረት እያደረገ ያለ ቢሆንም ከላይ እንደተጠቀሰው የተሰራጨው ብድር በወቅቱ ባለመመለሱ የተነሳ የየክልሎቹ በጀት  እየተቀነሰ ወደ አበዳሪውተቋም ካዝና በመግባቱ በክልሎች የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ ጫና እየፈጠረ ይገኛል፤

3.3. በብድርና እጅ በእጅ የሚገዙ የግብርና ግብዓቶች ፍላጎትን በተጠቃሚ ደረጃ በትክክል ካለመለየቱ የተነሳ ለተጠቃሚዉ የሚቀርቡ ግብዓቶች በተለይም የአፈር ማዳበሪያ ሲያድር/ሲከርም አልያም በማነስ የሚቀርብበት ሁኔታ መከሰቱ እንዲሁም የፍላጎት ማሰባሰቢያ ወቅት በፌደራል ደረጃ የብድር ጥያቄ ከሚመቻችበት ወቅት ጋር ያለመጣጣም፤

3.4. ለብድር ስርጭት የሚንቀሳቀሱ የባለድርሻ አካላት ለምሳሌ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በብድር ማስመለሱ ሂደት ዉስጥ የባለቤትነት ስሜት በመፍጠር ብድሩ በወቅቱ እንዲመለስ የሚያሳዩት ተሳትፎ ዉስን መሆኑ። ይኸውም ሊሆን


የቻለው ክልሎች የግብዓት ብድርንሙሉ በሙሉ ዋስትና እየሰጡ በመሆኑ በብድር ስርጭት እና ማስመለሱ ላይ ያሉ ባለድርሻ አካላት የሥራ ድርሻቸውን ተግተው እንዲሰሩ አያበረታታም፤

3.5. የግብርና ግብዓት ብድር አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መረጃ በየደረጃዉ በተደራጀ መልኩ በየተቋማቱ ተወራርሶ/ተረካክቦ ያለመያዝ፣ይህም በብድር ማስመለስ ስራ ላይ አሉታዊ ተጽኖ ማሳደሩ፤

3.6. አርሶ አደሮች የግብርና ግብዓት ብድር በወቅቱ መመለስ እንደሚገባቸዉ ያለማወቅ፣እንዲሁም እንዲመልሱ የሚያበረታታ ስርዓት ያለመኖሩ እና በብድር አሰባሰብ ተግባር ላይ የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት የሰበሰቡትን ገንዘብ ለአበዳሪ ተቋም በወቅቱ ባለማስገባታቸዉ በአጠቃላይ መልኩ በተበዳሪዉ በኩል ለከፍተኛ ተጨማሪ የወልድ ከፍያ መዳረግ፣ ይህንንም ችግር የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተገቢዉን የቅርብ ክትትል ባለማድረጋቸውከፍተኛ የግብርና ግብዓት ዉዝፍ ብድር መስተዋሉ፤

3.7. የግብርና ግብዓት ብድር በወቅቱ ባለመመለሱ ምክንያት ክልሎች ላይ ከፍተኛ ኪሳራ በማድረሱ አንዳንድ ክልሎች የብድር ዋስትና መስጠት በማቆማቸውና አርሶ አደሩ የግብርና ግብዓቶችን እጅ በእጅ እንዲገዛ በመገደዱ በግብርና ግብዓት አጠቃቀም ላይ ከፍተኛ ጫና አሳድሯል። ይህም ባለፈው ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተግባራዊነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳደሯል።

**እስከአሁን ድረስ በስራ ላይ ያለው የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ስርጭትእናአመላለስ የስራ ፍሰት**




ምንጭ: የአለማቀፍ ምግብ ፖሊሲ ምርምር ተቋም፣ 2012; ከቃለመጠይቅ የተወሰደ

## 4. የአዲሱ የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ሥርጭት እና አመላለስ ስርዓት

### 4.1. አጠቃላይ

ባለፉት አመታት በሀገሪቱ የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ስርጭት እና አመላለስ ስርዓት ዉስጥወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት ባለመኖሩ በርካታ ችግሮች ሲስተዋሉ ቆይተዋል፡፡ በዚህም የተነሳ በምርትና ምርታማነት እድገት እንዲሁም በሀገሪቱ የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ እድገት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ጫና ሲፈጥር መቆየቱ የሚታወቅ ነዉ፡፡

ይህንን መሳረታዊ ችግር ሥርነቀል በሆነ መልኩ ለማስወገድ የተስተካከለ፣ ወጥ የሆነ፣ ቀልጣፋ እና ተደራሽነት ያለዉ የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ሥርጭት እና አመላለሰ ስርዓት መዘርጋት አማረጭ የሌለዉ ተግባር በመሆኑ ቀጥሎ ያለዉ የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ሥርጭት እና አመላለሰ ስርዓት ተቀርጿል።

በተጨማሪም በሀገር ደረጃ የሚገኙት የብድር ገንዘብ አቅራቢ ባንኮች በበቂ ሁኔታና በአስተማማኝ መልኩ ለብድር የሚውለውን ገንዘብ ለገንዘብ አቅራቢ ተቋማትያመቻቹ ዘንድ ሀገራዊ የብድር ዋስትና ፈንድ እንዲመሰረት ይደረጋል፡፡

### 4.2. የአዲሱ የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ሥርጭት እና አመላለስ ስርዓት መርሆች

ከላይ እንደተጠቀሰዉ የግብዓት ብድር ስርዓት ችግሮችን ለመቅረፍ የተዘረጋዉ አዲስ ስርዓት ለመቅረጽ ከዚህ በታች የተቀመጡነጥቦች እንደመርህ አገልግለዋል።

- የብድር ስርዓቱ በገበያ መርሆች ላይ የተመሰረተ እና ቀጣይነት እንዲኖረዉ ማድረግ
- የክልል መንግስታት የብድር ዋስትናን የመስጠት ኃላፊነት ማስቀረትና የክልሎችን በጀት በየዓመቱ ላልተመለሰ ብድር ከማስቀነስ / ማስቀረጥ ማዳን፣
- የገንዘብ ተቋማት የግብርና ግብዓት ብድር ለአርሶ አደሩ እንዲያበድሩ እና እራሳቸዉ ብድሩን የማስመለስ ኃላፊነታቸዉን እንዲወጡ ለማበረታታት በከፊል የብድር ዋስትና እንዲያገኙ ማድረግ፣ ይኸውም የብድር ዋስትና ፈንድ የሚቋቋመዉ ከመንግስትና ከአጋር የልማት ድርጅቶች ትብብር እንዲመሰረት ማድረግ፣

- ህብረት ሥራ ማህበራትን ከብድር ማበደርና ማስመለስ ስራ በማዉጣት በዋነኛ ስራቸዉ እና የግብዓት አቅርቦት ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ማድረግ፤አርሶ አደሩ የምርት ግብዓቶችን በብድር ከማህበራት የሚወሰድበት አሰራርን አስቀርቶ አርሶ አደሩ ከገንዘብ ተቋማት (ማለትም በአካባቢው ከሚገኙ የብድርና ቁጠባ ተቋማትና የንግድ ባንኮች) ብድር በመውሰድ ከመህበራት የእጅ በእጅ ሽያጭ ወይም በቮውቸር የሚገዙበትን መንገድ መፍጠር፤

- የግብርና ግብዓት ፍላጎት ትምበያ በሚካሄድበት ወቅት  የህብረት ስራ ማህበራትን ሚና እንዲጎለብት ማድረግ በተጨማሪም ሳይሸጥ ለሚያድሩ ወይንም ለሚያንሱ የግብርና ግብዓቶች ተጠያቂ ማድረግ፤

- የግብርና ግብዓት ብድርን ለአርሶ አደሩ ለማቅረብ በሚመረጡት የገንዘብ ተቋማት ከፍተኛ የብድር አመላለስ ምጣኔ ያላቸዉ እንዲሆኑ ማድረግ ናቸዉ፡፡

## 4.3. የአዲሱ የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ስርጭትና አመላለስ ስርዓት ማብራሪያ

የዚህ የግብርና ግብዓት ብድር ሥርዓት ዋነኛ መገለጫ ሁሉም የባለ ድርሻ አካላት በቀጣይነት፣ በባለቤትነት እና በተቀላጠፈ መለኩ በሂደቱ ዉስጥ ያሉትን ተግባራት በተመጋገቢነት ለመከወን/ ለመተግበር በሚያስችል መለኩ የተቀረፀ መሆኑ ነዉ፡፡

የአገሪቱ የግብርና ግብዓት አጠቃቀም የሚፈለገዉን ያህል በብዛትና በተደራሽነት አኳያ ሲታይ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ሊገኝ ከቻለባቸዉ ዋነኛ ምክንያቶች አንዱ የብድር አቅረቦት አነስተኛ መሆን ነዉ፡፡ ይህም ሊሆን የቻለዉ ለአርሶአደሩ በሚመች መልኩ የብድር አገልግሎት ሊያቀርቡ የሚችሉ የገንዘብ አቅራቢ ተቋማት ተደራጅተዉ ወደ ስራ ባለመግባታቸዉ ነዉ፡፡ በዚሁ መሰረት በዚህ የግብርና ግብዓት ብድር ስርዓት የሚመለሱ ዋነኛ ነጥቦችም የባለድርሻ አካላትን ተግባርና ሀላፊነት በግልጽ በማስቀመጥ ሁሉም የባለ ድርሻ አካላት በቀጣይነት፣ በባለቤትነት እና በተቀላጠፈ መለኩ በሂደቱ ዉስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ ይሆናል፡፡

በዋነኛነት የገንዘብ አቅራቢ ተቋማት አቅማቸውን አደራጅተው ወደ ሥራው እንዲገቡ ማድረግ የሥርዓት ግንባታው መሰረታዊ ተግባር ይሆናል፡፡ የገንዘብ አቅራቢ ተቋማት ወደ ሥራው በስፋት ሲገቡ ለሚያጋጥማቸው የገንዘብ እጥረት ችግር በሀገር ደረጃ የሚገኙ ንግድ ባንኮችና ልማት ባንኮች የብድር አቅርቦት እንዲያደርጉላቸው ይደረጋል፡፡


### የተለያዩ ስጋት መቀነሻ መንገዶች

ከባለፉት ዓመታት ተሞክሮ በመነሳት የብድር ዋስትና ፈንድ ማቋቋም ብቻ ዘለቄታዊ መፍትሄ አለመሆኑን በግልጽ መረዳት ይቻላል። ይኸውም ከዚህ በፊት እንደታየው የማይመለስ የብድር መጠን በጣም ከፍተኛ ስለሆነ ፈንዱ ወዲያው ተመናምኖ የማለቅ እድሉ ከፍተኛ ነው። ስለሆንም የማይመለስ የብድር መጠንን ትርጉም ባለው ደረጃ ለመቀነስ በመጀመሪያ ለዚህ ችግር ምክኒያት የሆኑትን በመለየትና ለነዚህም ችግሮች ዘለቄታዊ ስጋት መቀነሻ መንገዶችን መቅረጽ ዓይነተኛ እና ዘለቄታዊ መፍትሄ ነው። በዚህም መሰረት ዋናዋና ስጋት መቀነሻ መንገዶች እንደሚከተለው በዝርዝር ተቀምጠዋል፦

- ቫዉቸር ሲስተም እና የተለያዩ ኤለክትሮንክ መረጃ ማስተላለፊያ መንገዶችን በመጠቀም በሰዉ እጅ የሚደረግ የገንዘብ ዝውውርን መቀነስ፤

- ለገንዘብ አቅራቢ ተቋማት ከብድር አመላለስ ስጋትን የሚቀንሱ  የተለያዩ ድጋፍና የቅርብ ክትትል ማድረግ፤
- የአርሶ አደሩን ስለቁጠባ ባህልእና ብድር ዕዉቀት ደረጃውን በተለያየ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻ በማሻሻል በዘርፉ በቂ ዕዉቀት እንዲኖረዉ ማድረግ፤
- የግብርና ግብዓት የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ አርሶ አደሮች በቡድን ዋስትና ማደረጀት፤
- ህብረት ሥራ ማህበራትን ከብድር ማበደርና ማስመለስ ስራ በማዉጣት በዋነኛ ስራቸዉ እና የግብዓት አቅርቦት ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ማድረግ፤
- አርሶ አደሩ በሁሉም ደረጃ የሰብል እንሹራንስ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፤
- የተረጋገጠ የገበያ ስርዓት ለአምራቾች እንዲኖር ማድረግ፤

## አዲሱ የግብርና ግብዓት ብድር አቀርቦት፣ ስርጭትና አመላለስ ስርዓት ስዕላዊ የስራ ፍሰተ




[1] ዋስትናው የሚያስፈልገው ብድር የማይመላስበት ሥጋቶችን መቀነስ ካልተቻለ ነው፡፡ በተጨብጭም አስተማማኝ የምርት ገበያ ካለ ዋስትናው አያስፈልግም

[2] የግዢ አፈጻጸምእንደየ ሰብሉ ዓይነትና ክልል ይለያያል ነገርግን ገዥ የግዢ ፍላጎቱን በደብዳቤ ወይምሊያሳውቅ ይችላል፡፡

## 4.4. የአዲሱ የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ስርጭትና አመላለስ የስራ ፍሰት

### 4.4.1. የግብዓት ፍሰት

- የግብርና ግብዓት ብድር ፍላጎት በመሰረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት፣ በልማት ሰራተኞች እና በየደረጃዉ ባሉ አስተዳደሮች ተዘጋጅቶ ይቀርባል፣
- የግብርና ግብዓት አስመጭና አምራች አካላት ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ግዢ በመፈፀም ወይም እንዲመረት በማድረግ በወቅቱ ግብዓት በክልሎች ፍላጎት መሰረት ለዩኒየኖች እና ለሰፋፊ እርሻ ባለቤቶች እንዲደርስ ይደረጋሉ፤
- ዩኒዬኖች ከግብርና ግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች የተረከቡትን ግብዓት ለመሰረታዊ ሕብረት ሥራ ማህበራት በፍላጎታቸዉ መሰረት ያስረክባሉ፤
- መሰረታዊ የሕብረት ሥራ ማህበራት ለተጠቃሚ አካላት በሚያቀርቡት የግብርና ግብዓት መበደሪያ ሰነድ /Voucher/ መሰረት ያሰራጫሉ፤እጅ በእጅ ለሚገዙትም ሽያጩን ያከናዉናሉ።

### 4.4.2. የግብርና ግብዓት ብድር ገንዘብ ፍሰት

- የገንዘብ አቅራቢ ተቋማት ለግብርና ግብዓት የሚውል የብድር ገንዘብ እጥረት ካጋጠማቸዉ ከመደበኛ ባንኮች የብድር ጥያቄ በማቅረብ ለዚሁ አገልግሎት የሚውል ገንዘብ መበደር ይችላሉ፤
- በተቋቋመው የብድር ዋስትና ፈንድ መሰረት መደበኛ ባንኮች ለገንዘብ አቅራቢ ተቋማት ለግብርና ግብዓት ብድር የሚውል ብድር ይፈቅዳሉ፤
- የግብርናግብዓትአምራቾችናአቅራቢድርጅቶችለግብርናግብዓትመግዣያ ብድር/ገንዘብያገኛሉ፤
- የግብርና ግብዓት ብድር ጥያቄ ለገንዘብ አቅራቢ ተቋማት በተጠቃሚዎች ይቀርባል፤

- የገንዘብ ተቋሙ ተጠቃሚዎችን ለብድር ብቁ መሆናቸውን ይገመግማል፤

- ለብድር ብቁ የሆኑ ተጠቃሚዎች ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት የገንዘብ አቅራቢ ተቋሙ በተጠየቀው የብድር ገንዘብ ልክ የግብርና ግብዓት መበደሪያ ሰነድ /Voucher/ በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች ይሰጣል፤

- የግብርና ግብዓት መበደሪያ ሰነድን /Voucher/ የያዙ ተጠቃሚዎች ከታደሰ የቀበሌ መታወቂያ አባሪ በማድረግ ሰነዱንለመሰረታዊ ኅ/ሥራ ማህበራት በማቅረብ በሰነዱ ላይ የተጠቀሰውንየግብዓት መጠንና ዓይነት ይረከባሉ፤

- የኅ/ሥራ ማህበራት ከተጠቃሚ ለተረከቡት ሰነድ /Voucher/ የኅ/ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች በማስረከብ በወሰዱት የግብርና ግብዓት መጠን መሰረት ያወራርዳሉ፤

- የኅ/ ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች ከመሰረታዊ የኅ/ ሥራ ማህበራት የተረከቡትን የግብርና ግብዓት ብድር ሰነድ /Voucher/ ወደ ገንዘብ ተቋማት በመውሰድ ሙሉ ወጪያቸውን እና ትርፋቸውን የሚሸፍን ክፍያ ብቻ ያወራርዳሉ። የገንዘብ ተቋሙ ከዛም የተቀረውን ሂሳብ አርሶ አደሩ ብድሩን ከከፈለ ብኋላ የወለድ ክፍያውን በመቀነስ ቀሪውን ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ ያደርጋል፤

### 4.4.3. የብድር ገንዘብ አመላለስ ፍሰት

- የየግብርና ግብዓት ብድር አገልግሎት ተጠቃሚዎች በወሰዱት የግብርና ግብዓት ብድር መጠን ብድር ስምምነት ሰነድ ላይ እንደተገለፀው በወቅቱ ለገንዘብ አቅራቢ ተቋማት የተበደሩትን ብድር በወቅቱ ገቢ ያደርጋሉ፤

- የገንዘብ አቅራቢ ተቋማት ለግብርና ግብዓት ብድር ለተጠቃሚው በሚያቀርቡበት ወቅት የገንዘብ እጥረት አጋጥሟቸው ከመደበኛ ባንኮች ተበድረው ከሆነ ወቅቱን ጠበቀው ተመላሽ ያደርጋሉ፤

## 4.5. ከአዲሱ የግብርና ግብዓት ብድር ሥርዓት የሚጠበቁ ውጤቶች

ይህ የግብርና ግብዓት ብድር ስርዓት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሲሆን ከዚህ ቀደም ያጋጠሙ ዋና ዋና የአሰራር ችግሮች ይፈታሉ፡፡ ለምሳሌ ፡-

- የክልሎችን በጀት በብድር ዋስትና የማስያዝ ሂደት በማስቀረት በየክልሉ ላይ ይከሰት የነበረው የልማት ዕቅድ የአፈጻፀም ችግር ይቃለላል፤ government collateral
- የግብርና ግብዓት ብድር አመላለስ ሂደት ባለቤት ያገኛል፣ በአዲሱ የብድር ስርዓት ለዘመናት ይታይ የነበረውንውዝፍ ዕዳ በወቅቱ ወደ አበዳሪ ተቋም የሚመለስበት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፤
- ለወደፊቱ የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት እና አጠቃቀም ላይ አወንታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፤
- የግብርና ግብዓት አጠቃቀምና ሽፋን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በአቅርቦትና በፍላጎት ላይ የተመሰረተ አሰራር ሆኖ ይቀጥላል፤
- በአጠቃላይ የአገሪቱን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የህዳሴ ጉዞን በማፋጠን የግብርናው ከፍለ ኢኮኖሚ ለእንደስትሪው ዘርፍ መሰረት እንዲሆን የበኩሉን አስተዋጾ ያበረክታል፡፡
- የገንዘብ ተቋማት ተደራሽነታቸውን ከጨመሩ አርሶ አደሩ ከግብዓት ብድር በተጨማሪ የቁጠባን ባህል ያዳብራል። ይኸውም በአገራችን ቁጠባን ለማዳበር በምንከተለው አቅጣጫ ላይ አዎንታዊ ተጽኖ ያሳድራል።

## 5. በግብዓት ብድር አስተዳደር ስርዓት የባለድርሻ አካላት ተግባር እና ኃላፊነት

ከዚህ ቀደም በነበረው የግብርና ግብዓት በድር ሰርዓት  ከዋናዋና ችግሮች አንዱ የሆነው የባለድርሻ አካላት በባለቤትንት በግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ስርጭት እና በተለይም በብድር አመላለስ ዙሪያ የነበራቸው ተሳተፎ ያልተጠናከረ የነበረ መሆኑ ነው፡፡

በግብርና ግብዓት በድር አቅርቦት፣ ስርጭት እና አመላለስ የስራ ሂደት ውስጥ እንደ ባለድርሻ አካላት (stakeholders) ከሚቆጠሩት/ከሚካተቱት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡-

5.1. በየደረጃው ያሉ የመንግስት መስተዳድር አካላት፣

5.2. በየደረጃው ያሉ የግብርና ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣

5.3. በየደረጃው ያሉ የህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ መ/ቤቶች፣

5.4. በየደረጃው ያሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መ/ቤቶች፤

5.5. የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ(ATA)፤

5.6. በየደረጃው ያሉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንኮች፣ልማት ባንክ እና የግል ባንኮች፣

5.7. የግብርና ምርት አቅራቢ ድርጅት

5.8. የአነስተኛ የገንዘብ አቅራቢ ተቋማት፣

5.9. በየደረጃው የተደራጁ የህብረት ሥራ ማህበራት፣

5.10. የግብርና ግብዓት ተጠቃሚ አርሶአደሮች እና የግል የእርሻ ተቋማት፣ ወዘተናቸው፡፡

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካላት (stakeholders) | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 5.1. | የመንግስት መስተዳድር አካላት | አርሶአደሮች እና የግል የእርሻ ተቋማት፣ የግብርና ግብዓት ብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ፤ |
| 5.1.1. | የፌደራል መንግስት | • በግብርና ግብዓት ብድር አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ የክልል መንግስታትን አፈጻፀም በመከታተል አቅጣጫ ይሰጣል፤<br>• ለግብርና ግብዓት ብድር የሚሆን በቂ ገንዘብ መኖሩእና ለብድር አቅራቢ ተቋማት በተገቢው ሰዓት እንዲደርስ አቅጣጫ ይሰጣል፤ |
| 5.1.2. | የክልል መንግሰታት በየደረጃው ባሉ መዋቀሮች | • የገንዘብ አቅራቢ ተቋማት በሚያወጡት የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ስርጭት እና አመላለስ መመሪያ መሰረት አስፈላጊዉን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤አፈፃም ይገመግማሉ፤<br>• የክልሉ አርሶ አደሮች እና የግል የእርሻ ተቋማትየግብርና ግብዓት አጠቃቀማቸዉ እንዲያድግ አስፈላጊዉን ድጋፍ ያደርጋሉ በተጨማሪም አፈፃም ይገመግማሉ፤<br>• በክልሉ የሚገኙ አርሶ አደሮች እና የህብረት ስራ ማህበራት ስለ ግብርና ግብዓት እና የብድር አጠቃቀም ያላቸው ግንዛቤ እንዲዳብር በሚደረግ ጥረት ድጋፍ ያደርጋሉ፤<br>• የግብርና ግብዓት ብደር ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ እና በብድር አመላለሱም ዙሪያ በሚደረግ ጥረት የሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት (stakeholders) የየበኩላቸዉን ተግባርና ኃላፊነት መወጣታቸዉን ይከታተላል ያስተባብራል በተጨማሪምአፈፃም ይገመግማሉ፤<br>• የግብርና ግብዓት አጠቃቀሙ በክልሉ ምርትና ምርታማነት እንዲሁም በክልሉ ኢኮኖሚ ላይ ያመጣዉን ዕድገት በመገምገም የአፈጻፀም ችግር ካለ ለሚመለከታቸዉ አካላት ተገቢዉንና ወቅታዊ የማስተካከያ አቅጣጫ |

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካላት (stakeholders) | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|---|
| | | ይሰጣሉ በተጨማሪም አፈፃም ይገመግማሉ፤<br>• ብሄራዊ የብድር ዋስትና ፈንድ እስኪቋቋም ድረስ የክልል መንግሰታት የግብዓት ብድር ዋስትና ለገንዘብ ተቋማት ማቅረብ መቀጠል አለባቸው። |
| 5.2. | በየደረጃዉ የሚገኙ የግብርና ሚኒስቴር መ/ቤቶች | አርሶ አደሮች እና የግል የእርሻ ተቋማት የግብርና ግብዓት አጠቃቀም በማሳደግና እና ምርታማነትን በመጨመር፣ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ሂደት የግብርናዉ ክፍለ አኮኖሚ ለኢንዱስትሪው ክፍለ አኮኖሚ መፈጠር መሰረት እንዲሆን ይሰራሉ፤ |
| 5.2.1. | የፌደራል ግብርና ሚኒስቴር | • የግብርና ግብዓት ብደርን አስመልክቶ ሀገራዊ ዉሳኔ በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ ይሳተፋል፤ ብድሩ እንዲፈቀድ ቴክኒካዊ ድጋፍ ያደርጋል፤<br>• የግብርና ግብዓቶችን ብድር በሚፈለገዉ ጥራትና ወቅት ለማቅረብ የሚያስችል አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤<br>• በየክልሉ ለሚገኙ አርሶ አደሮች እና የግል የእርሻ ተቋማት የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት በተገቢዉ መጠንና ወቅት እየደረሰ ስለመሆኑ እና የአመላለሱን አፈጻፀም ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤<br>• |
| 5.2.2. | የክልል ግብርና ቢሮዎች | • የክልሉን ግብርና ግብዓት ብደር ዕቅድ ከክልሉ ፋይናስ ተቋማት፣ መህበራትና መሰረታዊ ማህበራት ጋር በመሆን ገምግሞ ለፌደራል ግብርና እና ለክልሉ መስተዳድር ያቀርባሉ፣<br>➢ ትክክለኛ የግብዓት ፍላጎት እንዲተነበይ ያደርጋሉ፤<br>➢ ከሚመለከታቸዉ ጋር በመሆን የብደር ፍላጎት ይለያሉ |

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካላት (stakeholders) | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|---|
| | | • የማህበራትን በገበያ ላይ ተወዳደሪነት እና ቀጠይነት ለማረጋገጥ በየክልሉ የማህበራትን ፕሮፊት ማርጂንና የዋጋ ተመን ያዘጋጃሉ፤<br>• በወቅቱ የግብርና ግብዓት ለተጠቃሚዉ መድረስ እንዲችል የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ትራንስፖርተሮችን በማወዳደር ግብዓትን ወደ ክልሉ እንድጓጓዝ ያደርጋሉ፤<br>• የግብርና ግብዓት ብደርን አስመልክቶ ክልላዊ ዉሳኔ በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ ይሳተፋል፤ ብድሩ እንዲፈቀድ ቴክኒካዊ ድጋፍ ያደርጋሉ፤<br>• በፌደራል ደረጃ የተዘጋጀዉን የግብርና ግብዓቶችን ብድር  አሰራር ስርዓት መመሪያ ተግበራዊ ያደርጋል እንደ አስፈላጊነቱ የግብርና ግብዓቶችን ብድር  አሰራር ስርዓት መመሪያ በማዘጋጀት ተግበራዊ ያደርጋሉ፤<br>• በክልሉ አርሶ አደሮች እና የግል የእርሻ ተቋማት የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት በተገቢዉ መጠንና ወቅት እየደረሰ ስለመሆኑ እና የአመላለሱን አፈጻፀም  ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ፤ |
| 5.2.3. | የዞን ግብርና መምሪያ ጽ/ቤቶች | • የዞኑን ግብርና ግብዓት ብደር ዕቅድ ከዞኑ ፋይናስ ተቋማት ጋር በመሆን ገምግሞ ለክልል ግብርና እና ለዞኑ መስተዳድር ያቀርባሉ፣<br>• የግብርና ግብዓት ብደርን አስመልክቶ ዞናዊ ዉሳኔ በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ ይሳተፋል፤ ብድሩ በተገቢ መሰራጨቱና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዲመዘገብ  ቴክኒካዊ ድጋፍ ያደርጋሉ፤<br>• በፌደራልና እንደአስፈላጊነቱ በክልል ደረጃ የተዘጋጀዉን የግብርና ግብዓቶችን ብድር  አሰራር ስርዓት መመሪያ ተግበራዊ ያደርጋሉ ፤<br>• በዞኑ አርሶ አደሮች እና የግል የእርሻ ተቋማት የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት በተገቢዉ መጠንና ወቅት |

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካላት (stakeholders) | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|---|
| | | እየደረሰ ስለመሆኑ እና የአመላለሱን አፈጻፀም  ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ፤ |
| 5.2.4. | የወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች | • ከቀበሌ የመጣለትን የብድር ፍላጎት መሰርት በማድረግ የወረዳዉን ግብርና ግብዓት ብደር ዕቅድ ከወረዳዉ ገንዘብ ተቋማት ጋር በመሆን ገምግሞ ለዞን ግብርና እና ለወረዳዉ መስተዳድር ያቀርባሉ፣<br>• የግብርና ግብዓት ብደርን አስመልክቶ በወረዳዉ የዉሳኔ  ሀሳብ በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ ይሳተፋል፤ ብድሩ በተገቢ መሰራጨቱና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዲመዘገብ   ቴክኒካዊ ድጋፍ ያደርጋሉ፤<br>• በፌደራልና እንደአስፈላጊነቱ በክልል ደረጃ የተዘጋጀዉን የግብርና ግብዓቶችን ብድር  አሰራር ስርዓት መመሪያ ተግበራዊ ያደርጋሉ፤<br>• በወረዳዉ አርሶ አደሮች እና የግል የእርሻ ተቋማት የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት በተገቢዉ መጠንና ወቅት እየደረሰ ስለመሆኑ እና የአመላለሱን አፈጻፀም  ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ፤ |
| 5.3. | በየደረጃዉ ያሉ የህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ መ/ቤቶች | አርሶ አደሮች የግብርና ግብዓት አጠቃቀም እንዲያጎለብቱ ለማስቻል የሚረዱ ጠንካራ እና ብቁ የህብረት ስራ ማህበራትን በማስፋፋት ቀልጣፋ የግብይት ስርዓት እንመሰረት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፤ |
| 5.3.1. | የፌደራል የህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ | • የግብርና ግብዓት ብድር ዕቅድ በማደራጀት ያቀርባል፤<br>• የግብዓት ብድር በሚፈለገዉ ጥራትና ወቅት ለማቅረብ የሚያስችል አሰራር ስርዓት ግንባታ ላይ ይሳተፋል፤<br>• የመበደር አቅም ያላቸዉ እና  ጠንካራ የግብርና ግብዓት ግብይትና የብድር አስተዳደር አቅም የፈጠሩ የህብረት ስራ ማህበራት እንዲስፋፉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤ |

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካላት (stakeholders) | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|---|
| | | • የግብርና ግብዓት ብድር አሰተዳደር እና አጠቃቀም ዙሪያ የአቅም ግንባታ ሰራዎችን ይሰራል፤<br>• ለግበርና ግበዓት ግብይት አስፈላጊ የሆኑ አደረጃጀቶችንና መዛግብቶችን አሟልተዉ የሚገኙ የህብረት ስራ ማህበራት በየክልሉ እንዲጠናከሩ ድጋፍ ያደርጋል፤ |
| 5.3.2. | በየደረጃዉ ያሉ የህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ/ኤጀንሲ/ጽ/ቤቶች | • የመበደር አቅም ያላቸዉ እና ጠንካራ የግብርና ግብዓት ግብይትና የብድር አስተዳደር አቅምና ብቃት የፈጠሩ የህብረት ስራ ማህበራት እንዲስፋፉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ፣<br>• ለግበርና ግበዓት ግብይት አስፈላጊ የሆኑ አደረጃጀቶችንና መዛግብቶችን አሟልተዉ የሚገኙ የህብረት ስራ ማህበራት በየዞኑ፣በየወዳዉ እና በየቀበሌዉ እንዲጠናከሩ ድጋፍ ያደርጋሉ፤<br>• ግብርና ግብዓት ብድር አሰተዳደር እና አጠቃቀም ዙሪያ የአቀም ግንባታ ሰራዎችን ይሰራሉ፤<br>• አርሶ አደሮች ስለ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ያላቸው ግንዛቤ እንዲጎለብት ትምህርታዊ ቅስቀሳና ሥልጠና የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ድጋፍ በማድረግ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ትምህርታዊ ቅስቀሳና ሥልጠናም ይሰጣሉ፣፤ |
| 5.4. | በየደረጃዉ የሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መ/ቤት | የግብርና ግብዓት ብድር ለገንዘብ አቅራቢ ተቋማት እንዲፈቀድ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት (stakeholders) ጋር በመሆን አስፈላጊዉን ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ፤ |
| 5.4.1. | የፌደራል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር | • የግብርና ግብዓት ብድር ለገንዘብ አቅራቢ ተቋማት እንዲፈቀድ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት (stakeholders) ጋር በመሆን አስፈላጊዉን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤<br>• የግብርና ግብዓት ብደርን አስመልክቶ ሀገራዊ ዉሳኔ በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ ይሳተፋል፤ ብድሩ እንዲፈቀድ |

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካላት (stakeholders) | ተግባርና ኃላፊነት |
| --- | --- | --- |
| | | ቴክኒካዊ ድጋፍ ያደርጋል፤ |
| 5.4.2. | የክልሎች ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ | • የግብርና ግብዓት ብድር ለገንዘብ አቅራቢ ተቋማት እንዲፈቀድ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት (stakeholders) ጋር በመሆን አስፈላጊዉን ተግባራት ያከናዉናሉ፤<br>• የግብርና ግብዓት ብደርን አስመልክቶ ክልላዊ ዉሳኔ በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ ባለድርሻ አካላት (stakeholders) ጋር በመሆን ብድሩ እንዲፈቀድ ያደርጋሉ፤ |
| 5.5. | የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ (ATA) | የሀገሪቱን ክፍለ ኢኮኖሚ ከግብርና መር ወደ ኢንዳስትሪ መር በማሸጋገር ሀገሪቱን መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ አገሮች ተርታ ለማሰለፍ የሚያስችል ሀገራዊ አደረጃጀትና ስርዓትን በሚያሳልጥ መልኩ የግብርና ግብዓት ብድር ተደራሽነትንና መጠን ለማሳደግ የሚያስችል ከነባራዊ ሁኔታ ጋር ተስማሚ ስርዓት ይቀረጻል፣ |
| 5.6. | በየደረጃዉ ያሉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ የልማት ባንክ እና የግል ባንኮች | • በሚመሰረተዉ የብድር ዋስትና ፈንድ መሰረት ለግብርና ግብዓት ብድር የሚዉል ገንዘብ ለአነስተኛ የገንዘብ አቅራቢ ተቋማት ያቀርባሉ፤<br>• በሀገር ደረጃ በሚደረግ የግብርና ግብዓት ብድር የጋራ ኮሚቴ ሥራዎች ላይ ተሳትፎ ያደርጋል፤<br>• ስለ ግብርና ግብዓት ብድር አስፈላጊውን መረጃ ይይዛል፣ ያሰራጫሉ፤ |
| 5.7. | የግብርና ምርት አቅራቢ ድርጅቶች | • ለግብርና ግብዓት መግዣ በዩኒዬኖች ስም የሚመደብለትን ገነዘብ በወቅቱ፣ጥራቱን የጠበቀ የግብዓት ግገር በመፈጸም ያቀርባሉ፣<br>• በሀገር ደረጃ በሚደረግ የግብርና ግብዓት ብድር የጋራ ኮሚቴ ሥራዎች ላይ ተሳትፎ ያደርጋሉ፤<br>• ስለ ግብርና ግብዓት ብድር አስፈላጊውን መረጃ ይይዛል፣ ያሰራጫሉ፤ |

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካላት (stakeholders) | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 5.8. | ገንዘብ አቅራቢ ተቋማት | • ለግብርና ግብዓት ብድር አገልግሎት የሚዉል የገንዘብ ፍላጎት መረጃ በማሰባሰብ የብድር አገልግሎት እና ተዛማጅ ስራዎችን ያከናዉናል፣ የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥመዉ የብድር ጥያቄ ለአበዳሪ ባንኮች ያቀርባሉ፤<br>• ለብደር አገልግሎት የሚዉል የመበደሪያና የክፍያ ሰነዶች/Voucher/ በማዘጋጀት ጥቅም ላይ ያውላሉ፣<br>• ያሰራጨውን የግብርና ግብዓት ብድር በወቅቱ እንዲሰበሰብ ለማድረግ መረጃ ይይዛል፣ ስለአፈጻጸሙም በየደረጃው ላሉ የግብርና ልማትና የኅ/ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ መ/ቤቶች ርፖርት ያቀርባሉ፣<br>• አርሶ አደሮች ስለ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ያላቸው ግንዛቤ እንዲጎለብት ትምህርታዊ ቅስቀሳና ሥልጠና ይሰጣል፣ ሥራውንም ተግባራዊ ያደርጋሉ፤<br>• የግብርና ግብዓት ብድርን አስመልክቶ በየደረጃው በሚካሄዱ ውይይቶችና የምክክር መድረኮች ላይ ይሳተፋሉ፣ |
| 5.9. | በየደረጃዉ የተደራጁ የህብረት ስራ ማህበራት | የኅ/ሥራ ማህበራትን አባላት ተጠቃሚነት በሚያሳድግ ሁኔታ የግብርና ግብዓት ብድር በወቅቱና በተቀላጠፈ መልኩ እንዲቀርብ ያደርጋሉ፣ |
| 5.9.1. | የኅ/ሥራ ማህበራት ዩኔኖች | • የግብርና ግብዓት እና ብድር ፍላጎትን በመለየት ዕቅድ በማዘጋጀት ያቀርባሉ<br>• ለግብርና ግብዓት ማከማቻ የሚሆን ደረጃዉን የጠበቀ መጋዘን በዩኒየን እና በመሰረታዊ ኀ/ሥራ ማህበራት ደረጃ እንዲዘጋጅ በማድረግ የግብርና ግብዓቱን ከግብርና ምርት ማሳደጊያ አቅራቢ ድርጅት ተረክቦ በሚቀርበዉ የመረከቢያ ሰነድ መሰረት ለመሰረታዊ ኀ/ሥራ ማህበራት በወቅቱ ያስረክሉ፤<br>• የገንዘብ አቀራቢ ተቋማት ለተጠቃሚ አርሶ አደሮች ያሰራጨዉን የግብርና ግብዓት መግዣ ብድር ሰነድ /Voucher/ በተሰራጨው ግብዓት ዋጋ መጠን መሰረት ከመሰረታዊ ኀ/ ሥራ ማህበራት በመቀበል በማደራጀት ለየገንዘብ አቀራቢ ተቋማት በወቅቱ አቅርቦ ያወራርዳሉ፣ |

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካላት (stakeholders) | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|---|
| | | • የመሰረታዊ የኅ/ሥራ ማህበራት እና አባላት የግብርና ግብዓት ብድር አጠቃቀምና ግንዛቤ እንዲጎለብት የአቅም ግንባታ ሥራ ይሰራሉ፤<br>• አርሶ አደሮች ስለ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ያላቸው ግንዛቤ እንዲጎለብት ለሚሰጠዉ ትምህርታዊ ቅስቀሳና ሥልጠና ድጋፍ ያደርጋሉ፣ |
| 5.9.2. | የመሰረታዊ ኅ/ሥራ ማህበራት | • የግብርና ግብዓት ብድር ፍላጎት መረጃ በማሰባሰብ ያቀርባሉ፤<br>• ለግብርና ግብዓት ማከማቻ የሚሆን ደረጃዉን የጠበቀ መጋዘን በመሰረታዊ ኅ/ሥራ ማህበራት ደረጃ እንዲዘጋጅ በማድረግ የግብርና ግብዓቱን ከዩኔየኖች ይረከባሉ፣<br>• የግብርና ግብዓት ብድር ሰነድ /Voucher/ ከአርሶ አደሮች ተቀብሎ ለኅ/ሥራ ማህበራት ዩኔኖች በማቅረብ የግብርና ግብዓት ተረክቦ ለተጠቃሚዉ ያስረክባሉ፤<br>• የግብርና ግብዓት ብድር አስተዳደር የሚያገለግሉ የተለያዩ መሰረታዊ መዛግብትና ደረሰኞች ያዘጋጃሉ፣<br>• አርሶ አደሮች ስለ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ያላቸው ግንዛቤ እንዲጎለብት ትምህርታዊ ቅስቀሳና ሥልጠና የማስተባበር ሥራ ይሰራሉ፣ |
| 5.9.3. | በተለያየ የአደረጃጀት ደረጃ ያሉ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅ/ሥራ ማህበራት | • የአበዳሪነት ብቃታቸውን በማሳደግና በማጎልበት ልክ እንደ ሌሎች የገንዘብ አቅራቢ ተቋማት ሁሉ የሚከተሉትን ተግባራት ሊያከናውኑ ይችላሉ፣<br>• ለግብርና ግብዓት ብድር አገልግሎት የሚዉል የገንዘብ ፍላጎት መረጃ በማሰባሰብ የብድር አገልግሎት እና ተዛማጅ ስራዎችን ያከናዉናል፣ የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥመዉ የብድር ጥያቄ ለአበዳሪ ባንኮች ያቀርባሉ፤<br>• ለብደር አገልግሎት የሚዉል የመበደሪያና የክፍያ ሰነዶች/Voucher/ በማዘጋጀት ጥቅም ላይ ያውላሉ፣ |

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካላት (stakeholders) | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|---|
| | | • ያሰራጨውን የግብርና ግብዓት ብድር በወቅቱ እንዲሰበሰብ ለማድረግ መረጃ ይይዛል፣ ስለአፈጻጸሙም በየደረጃው ላሉ የግብርና ልማትና የኅ/ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ መ/ቤቶች ርፖርት ያቀርባሉ፣<br>• አርሶ አደሮች ስለ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ያላቸው ግንዛቤ እንዲጎለብት ትምህርታዊ ቅስቀሳና ሥልጠና ይሰጣል፣ ሥራውንም ተግባራዊ ያደርጋሉ፤<br>• የግብርና ግብዓት ብድርን አስመልክቶ በየደረጃው በሚካሄዱ ውይይቶችና የምክክር መድረኮች ላይ ይሳተፋሉ፣ |
| 5.10. | የግብርና ግብዓት ተጠቃሚ አርሶአደሮች እና የግል የእርሻ ተቋማት | • የግብርና ግብዓት ተጠቃሚ አርሶአደሮች በወቅቱ የግብርና ግብዓት ብድር ፍላጎታቸዉን በትክክል ያቀርባሉ፤<br>• አርሶ አደሮች ከገንዘብ ተቋማት የግብዓት ብድር ለመጠየቅ ማመልከቻ ቅፅ ይቀበላሉ፡፡ አርሶአደሮች ቅፁን በሞሙላት እንዲሁም የብድሩን አገልግሎት ለማግኘት መስፈርቱን ለማሟላት አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች ፣ ሰነዶች እና ሌሎችንም ማቅረብ አለባቸው። ከዚያም በኋላ የገንዘብተቋሙ በአርሶ በአደሮቹ ጥያቄ መሰረት የብድሩን ጥያቄ በመገምገም ውሳኔዉን ያሳልፋል። እንዲሁም የገንዘብተቋሙ የብድርአገልግሎት የሚያገኙትን አርሶ አደሮች ስምዝርዝር ይፋ ያደርጋል።<br>• ብድር የተፈቀደለት አርሶአደር ከማንኛውምገንዘብተቋምቅርንጫፍ ጽ/ቤትእንዲሁምበገበያቦታበሚገኙ ሳተላይትቅርንጫፎች ቮቸር ወይም የክፍያ ደረሰኝ ማገኘት ይችላል።<br>• አረሶአደሩቮቸሩን ካገኘበኃላበቮቸሩላይየተጠቀሰውንየግብዓትመጠንና ዓይነት ለማግኘትወደመሠረታዊ ሕብረትሥራማህበር ጽ/ቤትይሄዳል።መሠረታዊ ሕብረትሥራማህበሩ ከገንዘብተቋሙየተቀበለውንመረጃመሠረትበማድረግአረሶአደሩ ያመጣውን ቮቸር አፅድቆ የተፈቀደዉን የግብዓት መጠንና ዓይነት ለአረሶአደሩያቀርባል።<br>• አርሶአደሩብድሩን ከገንዘብተቋሙጋር ባለው ስምምነት መሠረትበተጠቀሰውየጊዜገደብውስጥብድሩን |

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካላት (stakeholders) | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|---|
| | | መልሶይከፍላል፡፡በተጠቀሰውየጊዜገደብውስጥክፍያውንሳይከፍል ቢቀር ቅጣት ይቀጣል፡፡ |

## 6. ማጠቃለያ

ይህየ ግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት፣ ስርጭትና አመላለስ መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻለው ሁሉም ባለድርሻ አካላት (stakeholders) የየራሱን ተግባርና ኃላፊነት ሲወጣ ይሆናል፡፡ወጥ የሆነ የግብርና ግብዓት ብድር ሥርዓት በመገንባት የአገራችንን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የግብርናዉ ክፍለ ኢኮኖሚ ለኢንዱስትሪዉ ክፍለ ኢኮኖሚ የመሸጋገሪያ ድልድይ በመሆን መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ አገራት ተርታ እንድትሰለፍ የዚህ መመሪያ ዋነኛ ዓላማነዉ፡፡